አገስት 1, 2024

የተወደዱ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ወላጅ

የልጅዎን ትምህርት ቤት የሚያገለግሉ የአውቶቡሶች መስመር የጊዜ ሠሌዳ አባሪ ተደርጓል። እባክዎ ለልጅዎ የተመደበውን ሰዓት፣ ቦታ እና የአውቶቡስ መስመር ቁጥር ያስተውሉ። ተማሪዎች አውቶቡሱ ከመድረሱ አምስት ደቂቃ በፊት ለመሳፈር በተመደበላቸው የአውቶቡስ መቆሚያ ቦታ ላይ ቀድመው ዝግጁ ሆነው መጠበቅ አለባቸው። አብዛኛዎቹ የአውቶቡስ መስመሮች የተነደፉት ተማሪዎች የት/ቤት አውቶቡስ ለመሣፈር አውራ መንገዶችን እንዳያቋርጡ ተደርጎ ነው። ይህ የአውቶቡስ መስመር "RSO" መግለጫ ላይ (በቀኝ በኩል ብቻ) ከአውቶቡስ ማቆሚያ ምልክት ቀጥሎ ተገልጿል። ወላጆች ሌላ ፌርማታ ካለ ሌላ የአውቶቡስ ማቆሚያ ለመጠቀም ብለው ልጆቻቸው መንገድ በማቋረጥ ለደህንነታቸው ስጋት እንዳይሆን መፍቀድ የለባቸውም። መንገድ ሳያቋርጡ በእነርሱ በኩል ምንም የአውቶቡስ ማቆሚያ የሌለ ከሆነ ወላጆች የዴፖ ማኔጀር ማነጋገር አለባቸው የአውቶቡስ መስመር ቁጥሮች በአውቶቡስ የጎን መስኮት ላይ ይታያሉ።

ከትምህርት ቤቱ 2 ማይል ርቀት ላይ የሚኖሩ ተማሪዎች የት/ቤት አውቶቡስ ትራንስፖርት አገልግሎት ለማግኘት ብቁ አይደሉም። ዕድሜአቸው የሚፈቅድ ከሆነ የእግር መንገድ ይኖራል። ጥያቄዎች ሲኖሩ ለትምህርት ቤትዎ የትራንስፖርት ኃላፊነት ለሚመለከተው ክላስተር ሱፐርቫይዘር መቅረብ አለባቸው። ከእርስዎ ትምህርት ቤት ወይም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድረ ገጽ ላይ የትራንስፖርት ክላስተር ኃላፊን የሚያገኙበት መረጃ ሊኖር ይችላል። ቀደም ሲል ተመድበው የነበሩ የአውቶቡስ ማቆሚያዎች ተወግደዋል ወይም በቁጠባ አብቃቅቶ የመጠቀም ሥራ ላይ ተመድበዋል። በተማሪዎች እና በወላጆች ላይ የሚደርሱ የማይመቹ ሁኔታዎችን ለመቀነስ እና ተገቢ አገልግሎት ለመስጠት የተቻለ ጥረት ሁሉ ይደረጋል። በድጋፍ የተገኘ የበጀት ዶላርን መቆጠብ ለመማሪያ ክፍሎች ተጨማሪ መገልገያዎችን ለማቅረብ ይረዳል።

የት/ቤት አውቶቡስ ፌርማታዎች በመስቀለኛ መንገድ ላይ በሚሆኑበት ጊዜ፣ ተማሪዎች ደህንነታቸውን ለመጠበቅ ከትራፊክ ርቀው፣ ከአውቶቡስ ማቆሚያው 150 ጫማ ርቀት ላይ መቆም አለባቸው። *በት/ቤት አውቶብስ ፌርማታዎች ላይ ወላጆች የልጆቻቸውን ዲሲፕሊን እና ደህንነትን የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው።* የት/ቤት አውቶቡሶችን የሚጠብቁ ተማሪዎች ከአየር ሁኔታ ለመጠለል ከፈለጉ በመኪና ፓርኮች እና ጋራዥ ውስጥ መቆም ይችላሉ። ይህ ተቀባይነት የሚኖረው፡- (1) መንገዱን የማያስቀይር ከሆነ፣ (2) የአውቶቡስ ማቆሚያ የማይጨምር ከሆነ፣ (3) በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ተቀባይነት ካለው፣ እና (4) ከመደበኛው ፌርማታ ጋር ተቀራራቢ ቦታ ከሆነ (ልዩ ሁኔታውን የማያ(ታ)ውቅ ተለዋጭ የአውቶቡስ ኦፐሬተር ተማሪዎቹን በቀላሉ ለማግኘት አመቺ ከሆነ) ብቻ ነው። እባክዎንያስታውሱ፡ የት/ቤት አውቶቡስ ኦፕሬተሮች ማቆም የተፈቀደላቸው በተመደበላቸው ፌርማታዎች ላይ ብቻ ስለሆነ ባልተፈቀደላቸው ማቆሚያዎች ላይ እንዲቆሙ አትጠይቁ። MCPS የአውቶቡስ ፌርማታዎችን ቁጥር በመገደብ ከፍተኛ የነዳጅ እና ሌሎች የአሰራር ቁጠባዎች መደረግ እንዳለባቸው ይገነዘባል።

አመቺ ያልሆነ የአየር ሁኔታ ለሁሉም ሰው ከባድ ችግሮችን ይፈጥራል። በዊንተር ወራትም ሆነ በዝናባማ ቀናት ተጨማሪ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አይቻልም፤ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ለአየር ሁኔታው ተስማሚ የሆነ ልብስ መልበስ አለባቸው። በሚያዳልጥ በረዶ እና በበረዶ ክምር ምክንያት አውቶቡሶች ወደተዘጋጀላቸው ፌርማታዎች በጊዜ መድረስ ካልቻሉ፣ ወላጆች ከአውቶቡስ ኦፕሬተሮች ጋር ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ እና በእነዚህ አካባቢዎች የሚኖሩ ተማሪዎች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በተለዋጭ ቦታዎች እንዲሳፈሩ ይበረታታሉ።

ተገቢ የሆነ የተማሪ ባህሪ ለሁሉም ሰው ደህንነት እና ምቾት አስፈላጊ ነው። ይህንን መልእክት ለማጠናከር ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ዘወትር ስለ ባህሪ እንዲወያዩ ይበረታታሉ።ሁሉም ተማሪዎች "*ህግ ኢያከበሩ መጓዝ*/Ride by Rules.።" በተሰኘ ዘመቻ ላይ የተዘረዘሩትን ህጎች መከተል ይጠበቅባቸዋል። የበለጠ መረጃ ለማግኘት እባክዎ ይህንን በይነመረብ ይጎብኙ: https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/transportation/rules/
እባክዎን ያስተውሉ፡ ተማሪዎች እንስሳትን፣ አልኮል፣ ትምባሆ፣ የጦር መሳሪያዎችን (አሻንጉሊት ወይም “የሚመሳስሉ” መሳሪያዎችን ጭምር)፣ ከመስታወት ብርጭቆ ነገር የተሠሩ እቃዎችን፣ ወይም የሚፈነዱ ነገሮችን ወደ ት/ቤት አውቶቡስ

ማምጣት የለባቸውም።

ተማሪዎችን ማጓጓዝ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ሁላችንም የበኩላችንን ድርሻ ከተወጣን ብቻ ነው። ለተማሪ ተሳፋሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ የመጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት የወላጅ እርዳታ እና ትብብር ያስፈልጋል።

ከማክበር ሰላምታ ጋር

Depot Manager

XXX:-xxx

አባሪ